# መቻቻል ይቻላል?

ከየንባ

ሰሞኑን ኤሊያስ ክፍሌ በሚያስተናግደው ድህረ ገጽ እና ተዛማጅ በሆነ የፓል ቶክ መታደሚያ ክፍል ቀን ከሌት ተቃዋሚ ድርጅቶችና ሁነኛ ኢትዮጵያውያን በተለየም ወያኔና መላ ጸረ ኢትዮጵያ ሐይላት የሚጠሉአቸው ግለሰቦች ሲከቸለቸሉ ሰንብተዋል። ዘመቻው ካሁን አሁን ይቀዘቅዛል ብንልም የሀምሌ ዝናብ ያህል ችክ ተብሎ ተያይዘውታል።

ቀደም ባለው ጊዜ ከሁነኛ ዜጎች ዶክተር ታየና ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ቅድሚያ ቦታ ነበራቸው። እንዲያው ለነገሩ የጀርባ የጸጉር ስንጣቂ ያክል አመል ቢገኝባቸው እኒህ ሁለት ግለሰቦች ምን በተባሉ ነበር ያሰኛል።ላለፉት ወራት በነዚህ ዜጎች ላይ የወረደው ተራ የመንገድ ስድቡና መክቸልቸሉ አበስሁ ገበሁ ያሰኛል። ሰሞኑን ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ግለሰቦች የነዚ ዱርየዎችና ምናልባትም አምስተኛ እረድፊኛ ሊሆን የሚችለው ማንን የሚደግፍ ማነን የሚቅቃወም ለመሆኑ ከልደቱ አእያሌው በቀር ልቦናው የማይታወቀው ፤ ለመልካም ሳይሆን ለከፋ ነገር ደራሹ ኤሊያስ ተጨምሮ የትግሉን ጎራ እንክርዳድ አጣቦት ይገኛል። በሰሞኑ በኤሊያስ ድህረ ገጽ አቶ ዳዊ ኢብራሂም ምንለማለት እንደፈለገ ባይታወቅም የድርጅት መሪንና ካገር እንድወጣ እረዳኝ ፤ ከኬኒያ ወዳውሮፓ ለመምጣት ያውሮፓን ኑሮ ጅማሮ አገዘኝ ባለው ድርጅት በኢሕአፓ ላይ የጭቃ ጅራፉን ሲያጮህም ተመልክተናል። ታዲያ ይህ ሰው ያቀረበው መጣጥፍ ከዚህ ግባ የማይባል ፍሬ ቢስ ሲሆን። ከሁሉም የሚያሳዝነውና የሚያስተዛዝበው ያጎረሰ እጅን ነካሽነቱ ነው። ነፍሱን ለማዳን አገር ለቆ ለስደት ሲዳረግ ላገርና ህዝብ ያረገው ነው በማለት ኢሕአፓ መተባበሩና መራሩን ስደት እዲቀልለት ያደረገውን ድርጅት አቶ ዳዊ ሳይውል ሳያድር አውሮፓ በገባ ማግስት በለመደበት ክህደት ትናንት በበለሳ ጎዶቹ ያደረገውን ደገመው። በሌሊት ተደብቆ የታገለበትን ድርጅትና አብረው ሲታገሉ የተሰው ጓዶቹን ደም ተራምዶ እጁን ሰጦ በሰላም መኖር ጀምሮ ነበር። ዎያኔ አዲስ አበባን ከጠቆጣጠረ በህዋላም የሚያውቃቸው ጓደኞቹ እነ በረከት ስምን፥ አዲሱ፥ ተፈራ ዋልዋ ስላሉ ለዚሁ ለሰራተኛው ኮንፌደረሽን ያመራር ቦታ አስቀምጠውት ነበር። በህዋላ የጠቡ መነሻ በቅጡ በማይታወቅ ግጨት ተነሳስቶ አቅፈው ደግፈው ካስቀመጡት ተነስቶ ነፍሱን ለማዳን ወጥቱአል። ዛሬ ጠንካራ ተቃዋሚን የሚሰድብላቸው ከረንት አፌርስ ፓልቶክ ብጤአቸውን ፈልገው ለኑዛዜ አበቁት።

ይህ ብቻ አይደለም ኤሊያስ ክፍሌ እንዳየሩ ባህሪ ተለዋዋጭ ኢትዮጵያዊ ትህትና በእጅጉ የሚጎለው ቀዥቃዣ ሲሆን የዛሬ ወዳጆቹን በአንድ ወቅት ብርሀኑ መዋን እና ዶክተር ብርሀኑ ነጋን ዙሮ እንዳደረሳቸው ድህረ ገጹን የሚጎበኙ ያስታውሱታል። ኤሊያስ በልደቱና በኤርትራ ግን የስብሃት/መለስን ያክል ቻሚና የማያወላውል አቁአም አለው።

በሰማኒያወቹ መጨረሻ ጀምሮ ያዘጋጀው የነበረ ኢትዮጵያን ሪቪው ወርሀዊ መጽሄትን ለማቆም የተገደደበት ዋና ምክንያት ይኸው የኤርትራን መገንጠል ይደገፉና ለመገንጠሉአም አቢይ ሚና የተጫወቱትን እነ አማረ ተክሌንና ሌሎችንም ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ለአገር ወገን ተቆርቁአሪ የሆኑ ምሁራንን በማሰደቡ ብሎም ያንድነት ሀይሎች በባለ ጊዜወች መሳቂአ መሳለቂያ መድረክ በመፍቀዱ ነበር። እዚህ ላይ ላሳይ የሞከርሁት ይህ አቅለ ቀሊል ግለስብ ምንም ቢሆን በተወሰኑ አቁአሞቹ ላይ ለውጥ የሌለው መሆኑን ያየ ሰው ለአንድ ሀይል ተቀጠሪነቱን እንዲገነዘብ በማለት ነው።

በሰሞኑ በዚሁ ድህረ ገጽ ለሰማእትነታቸው ወደር የሌላቸውን ብርቅየ የዚያ መንፈሰ ጽኑ ትውልድ ሰማእታቱን በጠባብ ብሄርተኞች ሲያሰድብ ተመልክተናል። ልክ እንዳለፈው ጊዜ አሁን ደሞ የ ኦነግ/የመራብ ሱማሌ ነጻነት ግንባርን የሚደግፉ ፤ ላንድነት የሚታገሉትን የሚያብጠለጥሉ መጣትፍች ሲያስተናግድ አስተውለናል። በእርግጥም ግለሰቡ ኢይትዮጵያን የሚያቃልሉ እንጅ የሚያከብሩ እንደማይወድ ያልተለወጠ ባህሪው መሆኑን ለማእላከት ሞክሬአለሁ። ታዲያ በሰሞኑ የጸረ ኢሕአፓ ዘመቻው ባያስገርምም ማናደዱ አልቀረም ለምን ብትሉኝ እንዲህ አይነት ቅጥረኞች አቸው በህዝባችንና ባገአችን ተንፈራጠው ሲያሻቸው በገፍ ወደማጎሪያ ይልካኡ ሲያሻ ይገላሉ በውጭ የወያኔ አለቆች በቀጠሩአቸ አምስተኛ እረድፈኞች የህዝብ ዎገኖችና ተቃዋሚ ድርጅቶች በየፓልቶኩ እራሳቸውን በደበቁ የቀይ ሽብር ተዋኒያንና በወያኔ ካድሬወች ጥምረት ሲብጠለጠሉ ይውላሉ። ይህን ማቆም የትግሉ አካል ይመስለኛል። በ 1995 እንደሆነውም ኢትዮጵያን ሪቪው መጋዚን በጠላት እያሰድበን ብሎ አንባቢ ያገገለለውን ያህ ዛሬም መደገም አለበት አለበለዚያ ዛሬ በነዶክተር ታየ በኢሕአፓ የጀመረው አፍራሽ ዘመቻ የወገን ቁጣን ካላየ በራሱ የሚገታ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።

ምንም እንኩአን በመልካም አሳቢ ግለሰቦች ቢጀመርም ከረንት አፌርስ ፓልቶክ ሩም የሚባለው የሳይበር ጦረኞች መታደሚያ ሌት ተቀን ሙያ ተግባሩ አንዳርጋቸው ጽጌ በሚያወጣላቸው የቀን ተቀን መነጋገሪያ ያገሪቱ ደግ አእሳቢ ዜጎች ሲብጠለጠሉበት የሚውል በረት ሆኑአል። ኢትዮጵያን ሪቪው የወጡ መጣጥፎችም እዚሁ ክፍል ይደገማሉ። የታዳሚው አይነትና የእድሜ ክልል የተለያየ ቢሆንም በአላማ ግን ተመሳሳይ በመሆናቸው የኢትዮጵያን አንድነት የሚጠሉት ተሰባሰበው ሲሳደቡ መሸቶ ይነጋል። ታዲያ ሰሞኑን የተያዘው መፈክር መቻቻል ይቻላል የሚል ነው። መቻቻሉ ከአንድነት ሀይሉ ተቃዋሚ ወገኖችና ድርጅቶች ጋር ሳሆን ከወያኔጋር ማለት ነው። ከዚህም በመነሳት ከላይ በጠቀስሁአቸው ግለሰቦች ላይ አንዴ ገንዘብ ወስደዋል ሌላ ጊዜ አንባገነን ናቸው ይሉናል። የኢሕአፓም ያአቁአም ጽኑነትን የሚያውቁት ጸረ ህዝብ ጸረ አንድነት ሀይሎች ላሰቡት ተንበርካኪ አላማ ገና ከፊታችን ይቆማል በሚል ስሌት ሰማእታቱን ሳይቀር በስም እያነሱ ሲሳደቡ ይውላሉ። ለዚህ ጸያፍ ተግባር ከጆርባ ገፊ አይዞህ ባይ አንዳርጋቸው የትናንቱ የወያኔ ምክትል ከንቲባ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ግለሰብ አንዳንድ የዋህን እንደሚሉት ያንድ ጊዜ ስህተት አይደለም ከወያኔ ያቆራኘው። እንዴው ለሬከርድ ያህል ፤ ከራሱ የእምነት ቃል ማረጋገጥ እንደቻልሁት ፤ በ 1970 አም ኢሕአፓ ሆኖ ወዳሲንባ አቅንቶ እንደነበር ይናገራል ታዲያ አእድዋ ወያኔወች ሰፈር ማን እንዳደረሰው ባይታወቅም ለሁለት አመታት ከህወሐት ሰራዊት ጋራ ተንቀሳቅሱአል። ወደ እንግሊዝ አገር ካቀና በህዋላ ወያኔ አዲስ አበባን እስኪያዘበት ጊዜ ለወያኔ የአውሮፓ ካድሬ ሆኖ ይሰራ እንደነበር ለታማኝ በሰጠው ቃለመጠይቅ ተናግሩአል። ሌላው ቢቀር የትግራይ ጠባብ ብሄርተኝነት አንገፍግፎኝ ለቀቅሁ ካለ በሁአላ ያሳተመው መጽሃፍ ጨርሶ ከወያኔ ያለመለያየቱን አመላካች ነው። ይህ ሰው ነው ዛሬ የተቃዋሚ መሪ ነው እያሉ ደጋፊወቹ ያዙን ልቀቁን ሲሉ የሚውሉለት። እኔን የሚያሳስበኝ ነገ ስብሀት ነጋ ወያኔን እቃወማለሁ ብሎ ቢወጣ ያው የለመደባቸው መንፈሱ መሪያችን በሚል በዚሁ በፈረደበት መንበርከክን በማያውቅ ድርጅትና በሰማእታቱ የሚደርሰው የስድብ ዶፍ ነው።

ዛሬ የምንታገላቸው ወያኔወች የቤት ስራቸውን ሰርተው ካድሬወቻቸውን እስከተቃዋሚ መሪነት በማድረሳቸው ሊደርስባቸው የሚገባው ዱላ ዞሮ በቁርጠኛ ያገር ልጆችና ድርጅቶች በመሆኑ ይህን የተደበላለቀ ሁኔታ ልናስተካክልው ካልቻልን፡ አይደለም 17 አመታት የተባለው የጠላቶች እቅድ ድፍን 100 የማይቀር ይሆናል። ታዲያ ዛሬ የወያኔ ሰላይ ልምራችሁ ሲለን ወግድ ካላልነው ነገ ጉግ ማንጉግ ኮተቱን ጨምሮ ምኒልክ ቤተ መንግስት ከገባ በህዋላ እየየው የሚበጅ አይደለም። አገሬን እወዳለሁ አንድነቱአን በትግል እመልሳለሁ ጠባብ ብሄርተኝነትን ላያዳግም ከህብረተሰባች ነቅየ እጥላለሁ የሚል የቆረጠ ተቃዋሚ ፤ ቅድሚያ ወዳጅ ጠላቱን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል ፤ አለዚያ ትግሉ ትርምስና የጠላት መቡአረቂያ ነው የሚሆነው። ዛሬ ዶክተር ታየ ኢሕአፓ የሚሰደቡበት ምክንያት ግንባራቸውን የማያጥፉ መሆናቸውን ጠላት ጠንቅቆ ስላወቀ ነው። በእርግጥ እኛ ከተባበርን ያያቶቻችንን ገድለ ታሪክ እንመልሰዋለን። ከጠላት መቻቻል ይቻላል የሚሉትን እንወቅ ሰርጎ ገቦች ናቸው። የልቁንም የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኤን የተሸከመበት ጀርባው ጎብጡአል። ከዚህ በሁአላ መሸከም በቃኝ ስላለ እንተባበረው እንጅ ከወያኔ ጋር መቻቻል አይቻልም መጎንበስ መረገጥ ነው። የህዝብ ትግል ይዘገያል እንጅ አቸናፊ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!